ኢጦብያ ኢጦብያ፣

የተውኩትን ነገር
ስለሌለው ጥበብ፣
አይ! አንት ባላገር!
አሁን ፈደል ታስብ!
በል ዝለቅ ሸዋ በር፣
በል ጣፈው በልብ!
አይተህ የኔን አገር።

ካሉህ አይጠየፍ
ይታይህ ሰገነት፣
አለች አንዲት አፋፍ፣
ኖራለች አንድ ቤት፣
ተደግፋ ያን ዛፍ፣
አይጠፋም ያ ዕምብርት፣
አፈሩን ከጫሩት።

ምን ትዝ አለህ ዛሬ፣
ምን አማረህ ወንድም፣
ዳቦ ቢሉህ ጥሬ ı
ስጋ ቢሉህ ዕርም!
ዋይ ምድር! አገሬ!
ሆነ ያንተ ወሬ።

እንዴት ብዬ ልግጠም፣
ቃሉ ጠፍቶ ስልቱ፣
አለኝ አልገጠም፣
ምን ይሆን ብልሀቱ፣
ማን ይረገም፣
መለስ በል መንግሥቱ፣
አልከኝ አሁን ግጠም፤
የቀረ እራዊቱ!

ተወኝ ይቅር ተወኝ፣
ጉድ ነው ዘንድሮ፣
ምስጢሩን አካፍለኝ፣
ተናደ አሉ አብሮ፤
ቀፎውን ነካክተው፣
ተነደፈ ሁሉም፣
ያልቃሉ፣ ጨርሰው፣
መቆምያ የለውም።

ያን ጊዜ ይባላል፣
ኢጦብያ ኢጦብያ፣
ሁሉም ይቀየራል፣
እስቲ ሃያ-ሃያ፣
ተው ምጣ፣ ተው ድረስ ı
ገስግሰህ በፈረስ።

Zeg Fanta
zegfantam@aol.com